# የምርቃን ስርዓተ ከበራ ኃይል በሰሜን ወሎ ማኅበረሰብ
# The Power of the Blessing Ritual Practices in the North Wollo Community

**ደምስ መሸሻ**[1]
**Demis Meshesha**

## አኅጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የምርቃን ስርዓተ ከበራ የሚያስገኘውን ማኅበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ስለሆነም የሰሜን ወሎ ማኅበረሰብን ፍልስፍና፣ አስተሳሰብ እንዲሁም አመለካከት ለመረዳት ላቅ ያለ ሚና ይኖረዋል፡፡ ጥናቱ በባህርይው ከአይነታዊ ምርምር የሚዋገን ነው፡፡ በተለያዩ መስፈርቶች ከተመረጡ የመረጃ አቀባዮች በምልከታ ፣ በቃለ መጠይቅ እንዲሁም በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰበውን መረጃ በሀቲታዊ ትንተና ስልት እየተተነተነ እና በክዋኔ ንድፈ ሃሳብ እየተመራ ዘልቋል ፡፡ የጥናቱ ግኝት የምርቃን ስርዓተ ከበራ አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ላይ የሚመረኮዝ ሲሆን ትኩረቱም ጤንነትን ፣ ተደማጭነትን ፣ አዱኛን ፣ የልጅ ፍሬን እንዲሁም ረጅም እድሜን የሚመኙበት ስርዓታዊ እሳቤ ነው ፡፡ የምርቃን ቱርፋት ተመራቂው ህይወቱን በአርያነት የመምራት፣ ማኅበራዊ ትስስርን የማጠናከር ፣ ቀና የመሆን እንዲሁም ሰዎችን ለመልካም ተግባር የማሰለፍ ኃይልን የሚያጎናጽፍ መሆኑ ተመላክቷል ፡፡ ከዚህም በተሻጋሪ የማኅበረሰብን ማንነት ፣ ስርዓት ፣ አኗኗር ፣ ልማድ ፣ ወግ ፣ ታሪክ ፣ ስነልቦና ፣ ርዕዮተ ዓለም እንዲሁም የህይወት ፍልስፍና ገላጭ ሆኖ የሚቀርብ መሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል ፡፡ ምርቃን በተለያዩ ዐውዶች ላይ የሚከወን ቢሆንም በዋናነት ግን ልጅ ሲወለድ ፣ አዲስ ቤት ተሰርቶ ሲገባ ፣ በግጭት አፈታት ስርዓት ፣ በእርሻ ስራ ፣ በሰርግ ፣ ቡና ሲጠጣ እንዲሁም በቱፋታ ስርዓት ላይ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ምርቃን ከአምላክ እና አላህ ጋር የመገናኛ ድልድይ መሆኑ ተመላክቷል፡፡ እንዲሁም እውነታ ላይ ሲመሰረት በልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል ቅቡል እንደሆነ ይታመናል ፡፡ የምርቃን ስርዓተ ከበራ ማኅበራዊ ፣ ስነ ልቦናዊ ፣ አስተዳደራዊ እንዲሁም አዱኛዊ አበርክቶዎች ያሉት መሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ ይሁን እንጂ ምርቃን ለልማት እንዲውል በማድረጉ ሂደት ውስጥ ውስንነት ታይቷል፡፡ በመሆኑም የሀገር ሽማግሌዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም የባህል ተመራማሪዎች ምርቃን ለልማት በሚውልበት ሁናቴ ላይ ትኩረት ቢሰጡ መልካም ነው፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** ማኅበራዊነት፣ ስርዓተ ከበራ፣ ስነልቦና፣ ኃይል፣ እሴት

[1] በወልድያ ዩኒቨርሲቲ የስነፅሑፍና ፎክሎር (የባህል ጥናት) መምህር: demismeshesha51@gmail.com

**Abstract**

The main purpose of this study is to examine the socio-psychological benefits of the blessing ritual practices in the North Wollo community. The study argues that studying blessing rituals plays a significant role in understanding the philosophy, thinking, and attitudes of a given community. To that end, a qualitative research approach and a descriptive research design were employed. The data were collected from selected informants through observation, interviews, and focus group discussions. The study used performance theory. The results of the study indicated that the ritual practice of blessing is based on logical thinking. Moreover, the ritual practice seeks health, honor, prosperity, and longevity. It is indicated that the product of blessing empowers the graduate to lead a noble life, strengthen social relations, be kind, and inspire people to do good deeds. The study also indicated that the blessing ritual is a reflection of the community''s identity, lifestyle, customs, traditions, history, psychology, ideology, and philosophy of life. Blessing is performed in various contexts; it is mainly mentioned when a child is born, when a new house is built, in conflict resolution systems, during agricultural work, at weddings, when drinking coffee, and during the Tufata system. It is indicated that the blessing is a bridge of communication with God and Allah. It is also believed to be endowed with supernatural powers when based on reality. Moreover, the study indicated that the blessing ritual has social, psychological, administrative, and economic benefits. However, there have been limitations in the process of using the blessing for development. Therefore, it would be good if elders, non-governmental organizations, and cultural researchers paid attention to the way in which the blessing is used for development.

**Keywords**: Power, Psychology, Ritual practice, Sociality, Value

## መግቢያ

ምርቃን በስነቃል ዘውግ ውስጥ የሚካተት ሲሆን ከማኅበረሰብ ልቦና ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ተመራቂ አካላት የማኅበረሰቡን ደንብ፣ መመሪያ፣ባህልና ወግ ለማክበር እና ለማስከበር የሚያስችላቸውን አቅም የመፍጠር ኃይል እንዳለው ይታመናል፡፡ በተሻጋሪነት ሰዎችን የላቀ ምግባር ባለቤት ለማድረግ እና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚያስችል መሆኑ ይገለጻል፡፡ እንዲሁም እሴትን የመትከያ፣ የማስጠበቂያ እና ግብረገብነትን የማጠናከሪያ ብልኃት በመሆን የማገልገል ሚና አለው፡፡

ምርቃን ተመራቂው ግለሰብ ወይም ቡድን በፈጣሪ ዘንድ የተወደደና የተመረጠ ሲሆን ምርቃቱ የፈጣሪ በረከት መሆኑን Barnhart (1995) አመላክተዋል፡፡ ምርቃን ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ረብ ያላቸው ባህላዊ ልማዶችን ማክበር፣በህግ መተዳደር፣

ታማኝና ታዛዥ መሆን፣ ደካሞችን መርዳት እንዲሁም ሰዎችን አክብረው ሲገኙ ከአንደበት በሚወጣ ገንቢ ቃላት ወይም በመልካም ድርጊታዊ ምላሽ በጎ ሰሪዎች የሚወደሱበት ነው፡፡ ምርቃን ያገኙት ግለሰቦችና ቡድኖች ባከናወኑት መልካም ተግባር የተበረከተልን ነው በማለት በመልካም ተግባራቸው እንዲቀጥሉ የማነቃቃት ኃይል አለው፡፡

የምርቃን ጥንታዊነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጣቀስ መሆኑን Dereke (1994) አመላክተዋል፡፡ የምርቃን ስርዓት በየትውልዱ ጉዞ ወስጥ የሚኖር ማኅበረሰባዊ ሀብት ነው፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ በጎ ነገሮች ለምርቃን መከሰት ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ መግባባትና መስማማት መመረቅን ያስከትላል፡፡ ሰዎች ባላቸው ሀይማኖት፣እምነት እንዲሁም ሚቶሎጂ ማኅበረሰቡ አምኖ የተቀበላቸውን የተጻፍ እና ያልተጻፉ ደንቦችን ማክበር ምርቃንን እንደሚያስገኝ ይታመናል፡፡ መልካም ተግባርን ማከናወን ምርቃን የሚያስገኝ መሆኑን Tzadok(2000) ገልጸዋል፡፡ ምርቃን እድሜ ጠገብና ቅቡልነት ባላቸው ሰዎች ሲከወን ይደርሳል ተብሎ እንደሚታመን Derek(1994), Hurriz(2006), Patricia(2004) ጠቁመዋል፡፡

ምርቃን ለፍትህ ስርዓት የራሱ ድርሻ አለው፡፡ እንዲሁም የማኅበረሰብን የአኗኗር ዘይቤ፣ ታሪክ፣ እምነት፣ ልማድና ስነልቦና ይገልጻል፡፡ ማኅበራዊ መስተጋብርን ያጠናክራል፡፡ በተጨማሪ ማኅበረሰብን ለልማት ያነሳሳል፤ በእሴቶች ላይ ተመርኩዞ ህይወትን የመምሪያ ይትባህል ያስገኛል፤ ግብረገብነትን ያዳብራል፤እንዲሁም የመከባበርና የመቻቻል መርህን የማጠናከር ኃይል አለው፡፡ ምርቃን አዎንታዊ ይዘት ያለው ሲሆን ሰዎች በሰዎች ላይ ዋስትና የማሳረፍ፣ በግብረገብነት የመገንባት፣ ባህላዊ እሴቶች እንዲጠበቁ የማድረግ፣ ማኅበራዊ መስተጋብርን የመመስረት እንዲሁም ልቦናን በማጠናከር በኩል ሚናው የጎላ ነው፡፡ ምርቃን እውነታ ላይ ሲመሰረት በልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ቅቡል እንደሆነ እና ወደ ተመራቂው የመድረስ ሀይል እንዳለው ይታመናል፡፡

የምርቃን አከዋወንና ስርዓቱ ከባህል ባህል ከሀገር ሀገር ይለያይ እንጂ ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች ምርቃን ያላቸው መሆኑን Hurriez (2006), Nizita (1993) አመላክተዋል ፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የምርቃን ማኅበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳን በሰሜን ወሎ ማኅበረሰብ ተተኳሪነት መመርመር ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ የምርቃን ምክንያቶችን መግለጽ፣ ምርቃን የሚቀርብባቸውን ዐውዶች መተንተን እንዲሁም የምርቃን ተምሳሌታዊ ሃቦችን መግለጽ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ የጥናቱን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ መረጃዎቹ ከቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሰብስበዋል፡፡ ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም በገላጭ የምርምር ስልት ተተንትኗል፡፡ ‹‹ገላጭ ጥናት ተመራማሪው የሚያጠናውን ባህሪ እንዳለ ትረካዊ በሆነ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ስለጉዳዩ ስዕል በሚፈጥር ሁኔታ ባልተጋነነ፣ ባልተሞካሸ፣ ባልተንኳሰሰና እውነታውን በማያደበዝዝ መልክ ለማቅረብ ያስችለዋል›› ያለው(1998)፡፡ ጥናቱ ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብን እየተከተለ የዘለቀ ሲሆን የአንድ ማኅበረሰብ አባላት ማንነታቸውን የሚገልፁበትና የሚያጠናክሩበት መሆኑን Sims

and stephens(2005) ገልፀዋል፡፡ በሌላ መልኩ Okpewho (1992) ክዋኔ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት እያገኘ የመጣ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ በምርቃን ክዋኔ ላይ የተመራቂውና የመራቂው መስተጋብር አስፈላጊ ነው፡፡ ልማዳዊ ስርዓቱን የሚመሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችና ልማዳዊ ክዋኔዎቹ በተግባር ሲመሩ ተሳታፊዎች ይኖራሉ፡፡

የምርቃን ስርዓተ ክዋኔ ተምሳሌታዊ ሃሳቦችን ያቀፈ ነው፡፡ Okpewho (1992) ተምሳሌት የአንድን ነገር ተጨባጭነት በሚያጎላ ሁናቴ የሚቀርብ እንዲሁም ረቂቁን ሃሳብ የሚያብራራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ምርቃን ለተመራቂው ሀሴትን፣ ስነልቦናዊ እርካታን እንዲሁም አካላዊና መንፈሳዊ በረከቶችን እንዲጎናጸፍ ዋስትናን ይመሰርታል፡፡

የመመረቅ ስልጣን ያላቸው በእድሜ አንቱታን ያተረፉ ሰዎች መሆናቸውን Patricia (2004) ጠቁመዋል፡፡ ሽማግሌዎች የአምላክና የአላህ ማደሪያ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ይከበራሉ፡፡ በእድሜ ከገፉት ባሻገር የሃይማኖት መሪዎች የመረቁት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በአፍሪቃ ውስጥ በእድሜ የገፉ፣ ማኅበራዊ ደረጃቸው የላቁ ሰዎችና የሀይማኖት መሪዎች የምርቃን ስርዓትን የሚመሩ መሆናቸውን Derek (1994), Hurreize (2006) አመላክተዋል፡፡ በሰሜን ወሎ ማኅበረሰብ አበጋሮች፣ ዘወልዶች፣ የደም አድራቂ ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች[2] እንዲሁም የእርፎ መረባ እናቶች የመረቁት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

የምርቃን ኃይል በትውልዶች ጉዞ ውስጥ የሚሸጋገር ነው ፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከወን ምርቃን እስከ ሰባተኛው ትውልድ ድረስ ይዘልቃል በሚል እምነት ይከወናል ፡፡ ዘር ይውጣልህ ፣ ሽንት ይውጣልህ እንዲሁም የሚጦር ልጅ ይስጥህ የሚሉ ምርቃኖች በማኅበረሰቡ ውስጥ ተዘውትረው ይተገበራሉ ፡፡ ከሀይማኖት ከሚቀዱ ምርቃኖች ውስጥ ‹‹ቤታችሁ የአብርሃም ይሁን ›› ፣ ‹‹ የእዮብን ትግስት ይስጣችሁ ›› እንዲሁም ‹‹ የአብርሃምና የሳራ ጋብቻ ይሁንላችሁ ›› የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው ፡፡ በተመራቂው የተከናወኑ ተግባራት በጎ ሆነው ሲገኙ መራቂዎቹ ውስጣዊ ደስታቸውን በምርቃን ይገልጻሉ ፡፡ የሰው ልጅ በመልካም ተግባሩ የሚመረቀው የአካልና የህሊና ንጥፈት እንዳይደርስበት በሚል እሳቤ ነው ፡፡

ምርቃን መራቂውንና ተመራቂውን የሚያስተሳስር ነው ፡፡ መራቂዎቹ ተመራቂዎቹ መልካም ነገር እንዲያገኙ የሚመኙበት ስርዓት ሲሆን ተመራቂዎቹም የተመረቁት እንዲደርስላቸው የሚመኙበት ስርዓት ነው ፡፡ ምርቃን በክዋኔ ይታቀፋል፡፡ በስርዓተ ክዋኔው ላይ የአካል ክፍሎች ተምሳሌታዊ ሚና አላቸው፡፡ ከአካል እንቅስቃሴ ውስጥ እጅና ጉልበትን መሳል ፣ እጅ መዘርጋት ፣ ከወገብ ጎንበስ ማለት እንዲሁም እጅን ወደ ልብ አቅጣጫ ማጠፍ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

[2]የእግዚያብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው ፡ እንዲህም አለው ፡፡እግዚአብሄር በራሴ ማለሁ ይላል ፤ ይህን ነገር አድርገሃልና ፡አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርከሃለሁ ፤ ዘርህም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባህር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ፤ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤ ዘፍ 22፣ 15-18

### የምርቃን ስርዓት የሚከወንባቸው ዐውዶች

ማኅበረሰቡ በዕለት ከእለት የህይወት መስተጋብራቸው ውስጥ ምርቃንን ይገለገሉበታል። ምርቃን የሚከናወንባቸውን ዐውዶች እና ፋይዳዎችን መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ገልጸውታል። ‹‹ ምርቃን በሰርግ ላይ፣ ልጅ ሲወለድና አዲስ ቤት ተሰርቶ ሲገባ፣ ከአዝመራ ጋር ተያይዞም እንዲሁም ሰዎች ተሰባስበው ቡና ሲጠጡ ይመረቃል። ምርቃን ከበሽታ ይሰውራል እንዲሁም መቅሰፍትን ይመልሳል››[3] በተለያዩ ማኅበራዊ ዐውዶች ላይ የምርቃን ስርዓት የሚከወን ሲሆን ከሁነቶች ውስጥ በሽምግልና ስርዓት፣ አዲስ ቤት ተሰርቶ ሲገባ፣ ልጅ ሲወለድ፣ ቡና ሲጠጣ፣ በቱፋታ፣ በሰርግ እና በሀዘን ስርዓት እንዲሁም በዕለት ከእለት ህይወት ውስጥ መልካም ተግባር ሲከወን እና ከአንደበት መልካም ቃል ሲወጣ ምርቃን ይከወናል። በተጨማሪም በወዳጃ ስርዓት ላይ ምርቃን ይተገበራል። አሰፋ (2017) ወዳጃ በጋራ የሚከወን ስርዓት ሲሆን በማኅበረሰቡ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመዋጋት ወይም ለመቀልበስ እና በበሽታ አምጪ መንፈሳዊ ሃይሎች የሚሰቃዩ ህሙማንን ለማከም፣ የተፈጥሮ ችግሮችን፣ ማኅበራዊ ግጭቶችንና ኢኮኖሚያዊ መሰናክሎችን ለመፍታት ሚና ያለው መሆኑ ጠቁመዋል። እንዲሁም ሥነ ልቦናዊ እፎይታን የማስገኘት እና ማኅበራዊ ትስስርን የማጠናከር ተግባር ያለው መሆኑን አመላክተዋል።

የምርቃን ስርዓት ከሚከወንባቸው ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ[4] ። በአካባቢውና ሀገር ላይ ጦርነት እንዳይከሰት ፣ ድርቅ እንዳይሆንና ወረርሽኝ እንዳይመጣ ፣ የታመሙ ሰዎች ከህመማቸው እንዲፈወሱ ፣ ምጥ የተያዙ እናቶች በሰላም እንዲገላገሉ ፣ ዝናብ ሲቀር ዝናብ እዲመጣ ፣ የግድያ እርቅ እንዳይፈርስና እንዲፀና ፣ አዲስ የተሰራ ቤት መደሰቻ እንዲሆን ፣ ትዳር መስራቾች ትዳራቸው መልካም እንዲሆንና ልጆች ወልደው የሚስሙ እንዲሆኑ የምርቃን ስርዓት ይከወናል ። በምርቃን ክዋኔ ወቅት መራቂዎቹ በአንድ በኩል ተመራቂዎቹ ደግሞ በሌላ በኩል ፊት ለፊት ሆነው ይከውናሉ ። ፊት ለፊት መቀመጣቸው ልብ ለልብ መገናኘታቸውን አመላካች እሳቤ ነው ። በተለያዩ ዐውዶች ላይ የሚቀርቡ የምርቃን አይነቶችና እሳቤያቸውን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል።

### ልጅ ሲወለድ የሚበረከት ምርቃን

ልጅ ፀጋ ነው ፤ ስም ያስጠራል ፣ ዘር ይተካል እንዲሁም የሞት መድሃኒት ተደርጎ ይወሰዳል ። የሰሜን ወሎ ማኅበረሰብ ልጅ ሲወለዱ በምርቃን ይቀበላሉ ። እናቶች ልጅ ሲወልዱ የሚቀርብ ምርቃንን መረጃ አቀባዮቹ እንዲህ ገልፀውታል ‹‹የወለዳችሁት ይባረክ ፣ የሚያድግ ልጅ ይስጣችሁ ፣ ቤተሰቡን የሚጦር ሀገሩን

[3] ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ ሀያት አሊ ሀብሩ ወረዳ 2/3/2014 ዓ.ም
ቃለ መጠይቅ ሸህ አደም ጉተማ ፣ ሀብሩ ወረዳ 2/3/2014 ዓ.ም
[4] ቃለ መጠይቅ አቶ አዳነ አገዘ ፣ ቆቦ ወረዳ 11/7/2014 ዓ.ም

የሚጠቅም ልጅ ይሁንላችሁ እንዲሁም ከመቅሰፍት ይሰውርላችሁ በማለት የምርቃን ስርዓት ይከውናሉ[5] ።

ከላይ የቀረበው እሳቤ የሚጠቁመው የተወለደው ልጅ በሰላምና በጤና አድጎ ራዕይ ያለው ዜጋ እንዲሆን ፣ ሰዎችን የሚረዳና የሚያከብር እንዲሁም ታታሪ ሆኖ የማየት ተስፋቸውን የገለጹበት ነው ። ወላጆች የልጅ ፍሬ በማግኘታቸውና ምርቃኑን በመቸራቸው ሀሴትን ያሰርፃሉ ። ስነልቦናዊ እርካታን ይጎናፀፋሉ ። ተመራቂዎቹ እጃቸውን በመዘርጋት ወደ ላይ ቀና ብለው እያዩ እንዲሁም ከአንገታቸው ደፋ ብለው ምርቃኑን ይቀበላሉ ። እጅ በተለይም የተዘረጋ እጅ የመቀበያ ተምሳሌትነት አለው ። ወደ ላይ ቀና ማለታቸው ደግሞ የምርቃኑ ቱርፋት የሚገኘው ከልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል መሆኑን የሚያመላክት ነው ። የተዘረጋውን እጅ ወደ ልባቸው አቅጣጫ አጠፍ እያደረጉ አሜን ማለታቸው ደግሞ የምርቃቱ በረከት ወደ ልቦናቸው እንዲደርስ የሚገልጹበት ተምሳሌት ነው ። ከአንገታቸውን ደፋ ማለታቸው ደግሞ የአክብሮት መግለጫ ትዕምርት ነው ።

የልጆች መባረክ ለቤተሰብ ፣ ለአካባቢና ለሀገር ቱርፋቱ ይደርሳል የሚል አስተሳሰብ በማኅበረሰቡ ውስጥ የነገሰ ነው ። ምርቃን ለተመራቂዎች ይደርሳል የሚለው ሃሳብ የነገሰበት ምክንያት የተመረቀ መልካም ነገር ይገጥመዋል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው ። ከዚህም ባሻገር የሃይማኖታዊ አስተምሮዎችን መሰረት በማድረግ ነው።

## አዲስ ቤት ተሰርቶ ሲገባ የሚከናወን ምርቃን

ቤት መጠለያ ፣ ማረፊያ ፣ መልካም ነገር ሲፈጠር መደሰቻ ፣ አሳዛኝ ነገር ሲገጥም ደግሞ ሀዘንን ማውጫ ነው ። በማኅበረሰቡ ህይወት ውስጥ ቤት የሚሰራው በጋራ ሲሆን አዲስ ቤት ተሰርቶ ሲጠናቀቅ የምርቃን ስርዓት ይከወናል ። ቤት ሰሪዎች አዲስ ቤት ሰርተው ሲገቡ የሚቀርብ ምርቃንን መረጃ አቀባዮቼ እንዲህ ገልፀውታል ‹‹ ቤት ለእንቦሳ፣ የዓለም የደስታ ቤት ይሁንላችሁ ፣ህጻናት የሚቦርቁበት እንዲሁም እንቦሶች የሚፈነጩበት ቤት ይሁን በማለት ይመረቃል [6]››

ከላይ የቀረበው ምርቃን እሳቤ አዲሱ ቤት ሰላም የሰፈነበት እንዲሆን ምኞታቸውን የገለፁበት ሲሆን የሰላም ፋይዳ አርሶ ለማምረት ፣ ነግዶ ለማትረፍ እንዲሁም ወልዶ ለመሳምና ለማሳደግ ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን የሚጠቁም ነው። በተጨማሪ አዲሱ ቤት ህጻናት ደስታን እየተጎናፀፉ የሚያድጉበት ፣ የተቸገሩ ሰዎች የሚያርፉበት ፣ የተራቡና የተጠሙ ሰዎች የሚበሉበትና የሚጠጡበት ቤት እንዲሆን ምኞታቸውን የገለጹበት ነው ።

---

[5] ቃለ መጠይቅ አቶ ደረስ ቸኮለ ፣ ቆቦ ወረዳ 19/9/2014 ዓ.ም
[6] ቃለ መጠይቅ ሽህ አደም ጉተማ ፣ ሀብሩ ወረዳ 14/6/2014 ዓ.ም
ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ ሃያት አሊ ፣ ሀብሩ ወረዳ 14/6/2014 ዓ.ም

ቤት መሰባሰቢያ በመሆኑ መተሳሰብን ፣ መረዳዳትን ፣ መተዛዘንን እና አብሮነትን ይመሰርታል ፡፡ እንዲሁም ማኅበራዊ መስተጋብርን ያጠናክራል ፡፡ በተሻጋሪነት ልጆች መልካም ምግባርን የሚቀስሙበትን ዐውድ ያመቻቻል ፡፡ አንድ ግለሰብ ቤት ሲሰራ የአካባቢው ሰዎች በተለያየ መልኩ እገዛ ያደርጋሉ ፡፡ እገዛውም የተወሰኑ ሰዎች እንጨት ፣ የተቀሩት ደግሞ ሳር (ሰንበሌጥ) ሌላኞዎቹ ሰዎች ደግሞ ለቤቱ መስሪያ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ይዘው መጥተው የግለሰቡን ቤት ይሰራሉ ፡፡ ማኅበረሰቡ ተግባራትን በጋራ ማከናወናቸው ያላቸውን የመረዳዳት ባህል እንዲሁም የመተሳሰብ እሴታቸውን የሚያመላክት ነው ፡፡ ቤት(ጎጆ) ከመጠለያነት ባሻገር የትዳር መያዝ ወኪል ይሆናል ፡፡ ትዳር ቤተሰብን ፣ ቤተሰብ ደግሞ ሀገርን የመግለጥ ሚናን ይወጣል ፡፡ ማኅበረሰቡ በጋራ ቤት መስራታቸው የመተባበርና የመረዳዳትን አስፈላጊነት አፅንኦት የሚሰጡበት ነው ፡፡

በሌላ መልኩ የግለሰቡን ቤት ለመስራት በሚሰባሰቡበት ወቅት ቤቱን ከመስራት ባሻገር ስለ እርሻ ፣ እንስሳት ፣ ሰላም እንዲሁም ስለ ማኅበራዊ ኑሯቸው መረጃ የሚለዋወጡበት ዐውድ ነው ፡፡አዲስ ቤት የሚያሰሩት ግለሰቦች አቅማቸውን ባገናዘበ መልኩ ቤታቸውን ለሰሩላቸው ዘመድና ጎረቤት ምግብና መጠጥ ያዘጋጃሉ ፡፡ ቤቱን ሲሰሩ የዋሉት ሰዎች በአዲሱ ቤት ውስጥ የምግብና የመጠጥ ግብዣ ይደረግላቸዋል ፡፡ ምርቃን ይመራረቃሉ ፡፡ አስረጂ እንሆ [7]፡-

| መራቂ | ተመራቂ |
|---|---|
| ኑሮህ ሰላም ይሁን | አሜን |
| በረተህ ሙሉ ይሁን | አሜን |
| ጎተራህ የማያልቅ ይሁን | አሜን |
| ቀዬህ የተባረከ ይሁን | አሜን |
| ላምህ መንታ ወላድ ትሁን | አሜን |
| በሬህ የማይደክም ይሁን | አሜን |
| ግንባርህ የማይደፈር ይሁን | አሜን |
| የረገጥከው እርጥብ ይሁን | አሜን |
| የመረቅኸው ምሩቅ ይሁን | አሜን |
| የረገምከው እርጉም ይሁን | አሜን |
| ጫካውም ዱሩም ይታዘዝህ | አሜን |
| እንስሳቱ ይታዘዝልህ | አሜን |

የሰው ልጅ በየትኛውም የህይወት አቅጣጫ ውስጥ መልካም ነገሮች እንዲገጥሙት ይመኛል ፡፡ ምኞቱ እውን ሆኖ ለማየት ካለው ፍላጎት የተነሳ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

አንዳንድ ጊዜ በተለያየ ምክንያት ተለፍቶ ውጤቱ መና ይሆናል ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የስራ ውጤቱ መልካም ቱርፋትን ያስገኛል ፡፡ ይህ ከመባረክና ከመመረቅ ጋር ትስስር እንዳለው ይታመናል፡፡ የሰው ልጅ የህይወትን ትርጉም

[7] ቡድን ተኮር ውይይት ፣ ቆቦ ወረዳ 20/9/2014 ዓ.ም

ከሚያጣጥምባቸው ነገሮች መካከል ትዳር መስርቶ የአብራክን ክፋይ መሳም ፣ ጋጡ በፍየልና በግ ተሞልቶ ማየትና ከብቶች በረት ሙሉ ሆነው መመልከት ተጠቃሽ ናቸው ። እንዲሁም እህል የሚያጠራቅምበት ጎተራው ያልጎደለ ፣ በሰዎች ዘንድ የተከበረና ከበረከት ጋር የተገናኘ ፣ የመረቀው ምርቃን እንዲሁም የረገመው እርግማን በሰዎች ዘንድ የሚደርስ እንዲሆን ምኞታቸውን የገለፁበት ነው ። ከሰው ልጆች ባሻገር አራዊቱ ፣ ዱሩና ጫካው ሁሉ የሚታዘዙለትና የሚገዙለት የልዕለ ተፈጥሮ ግብር በእሱ ላይ እንዲያድር ምኞታቸውን ያሻገሩበት እሳቤ ነው።

## በደም እርቅ ላይ የሚቀርብ ምርቃን

በማኅበረሰቡ ህይወት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶች ወደ ግድያ ሊሻገሩ ይችላሉ ። በደም ማድረቅ ሂደቱ ውስጥ ከሀገር ሽማግሌዎች ጎን የእርፎ መረባ እናቶች ሚና አላቸው ። የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች የማያመረቅዝ እርቅ እንዲፈፅሙ አበጋሮች ፣ ዘወልዶች ፣ ደም አድራቂ ሽማግሌዎች እና የእርፎ መረባ እናቶች ይመርቃሉ ። የእርፎ መረባ ስርዓት የሚከወነው በአውጪና ተቀባይ መካከል ሲሆን በዜማ የሚቀርብ ነው ። ስርዓቱ በሚከወንበት ዐውድ ላይ እርጥብ ሳር ይቀርባል ። የእርጥብ ሳር ተምሳሌት የመልካም እድል መግለጫ ነው ። በተለያየ መልኩ የተፈጠሩ ግጭቶችን አበጋሮች ፣ ዘወልዶች ፣ ደም አድራቂ ሽማግሌዎች ሲፈቱ የእርፎ መረባ እናቶች ቆቲ (ቀጭን ዘንግ) ይዘው ይቀርባሉ ። የሚይዙት ቆቲ ከሰሳ እንጨት የሚዘጋጅ ሲሆን የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ለስላሳ እና የእጅ ወዝ በቶሎ የሚለምድ በመሆኑ ነው ። መለስለስና ወዝ መላመድ መስተጋብርን ፣ ፍቅር እና ሰላምን ገላጭ ሆነው ይቀርባሉ ።

አስረጂ እንሆ[8] :-

| መራቂ | ተቀባይ |
|---|---|
| እርፎ መረባ | መረባ |
| ነዋሪዎች ጤና ይሁኑ | መረባ |
| ጠብና ጥላቻ ከእኛ ይራቅ | መረባ |
| እርቀ ሰላም ይውረድ | መረባ |
| ደጁ ሰው አይናፍቅ | መረባ |
| ከብቱ ውሉ ይግባ | መረባ |
| የሞተው ጀነት ይግባ | መረባ |
| ያሉት ልጆች ይደጉለት | መረባ |
| ለሞተው ነፍሱን ይማር | መረባ |
| ደም መቃባትስ አይበጀን | መረባ |
| ሰላም ደግነት ይበጀን | መረባ |
| ደም ይድረቅልን? | መረባ |
| ደግሞ በሰርግ እንጂ በግድያ አንገናኝ | መረባ |
| እርቅ ይውረድ | መረባ |

[8] ቡድን ተኮር ውይይት ፣ ጉባላፍቶ ወረዳ 8 /8/2014 ዓ.ም

አበጋሮች ፤ ዘወልዶች ፤ ደም አድራቂ ሽማግሌዎች እና የእርፎ መረባ እናቶች በሚችና በገዳይ ቤተሰቦች መካከል ሰላም እንዲወርድና የደም መመላለስ ድርጊት እንዳይኖር ይመርቃሉ ። ምርቃን በደል በደረሰባቸው ሰዎች ልቦና ውስጥ እንዲዘልቅ ይተጋሉ እንዲሁም በምርቃኑ የተገለጸውን መልካም ነገር በተግባር እንዲኖሩት ይሻሉ ። በህይወት ያሉት ሰዎችም ሳይገዳደሉና እንቅፋት ሳይገጥማቸው እንዲኖሩ ያላቸውን ተስፋ ‹‹ነዋሪዎቹ ሰላም ይሁኑ ›› በማለት ይመርቃሉ ። በደል በደረሰባቸውና በደል ባደረሱት ሰዎች መካከል ግጭት ፤ ግድያ ፤ጥላቻ ፤ ጭቅጭቅና ንትርክ እንዳይከሰት ይለምናሉ ። ሰላም የሰፈነበት ፤ አካባቢው ሰው የሚውልበት እንዲሁም በግጭቱ ምክንያት ሰዎች ያልተሰደዱበት ቀዬ እንዲሆን ይሻሉ ።

ደጃፋቸው በሰዎች የተሞላ እንጂ ባዶ እንዳይሆን የሚመርቁበት ዐውድ ነው ። የተገደለው ሰው ነፍሱ እንዲትለመልም ያላቸውን ፍላጎት ለመግለፅ ‹‹ የተገደለው ሰው ነፍሱ ጀነት ትግባ ›› በማለት ይመርቃሉ ። የሚች ልጆች አድገው ቤተሰብን ፤አካባቢንና ሀገርን የሚጠቅሙና መልካም ምግባር ያላቸው እንዲሆን ‹‹ ያሉት ልጆች ይደጉለት ›› በማለት ምኞታቸውን ይገልጻሉ ።

በሚችና በገዳይ ቤተሰቦች መካከል ነፍስ መጠፋፋትና በደም መቃባት በየትውልድ ጉዞ ውስጥ የሚሻገር በመሆኑ የተወገዘ እና የረከሰ ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ ። በደም ከመቀባባት ይልቅ ሰላም፤ ደግነት ፤ ርህራሄና መተሳሰብ የሚበጅና አስፈላጊ መሆኑን ‹‹ ደም መቃባትስ አይበጀን ፤ ሰላም ፤ ደግነት ይበጀን ›› በማለት ይመርቃሉ ። አበጋሮች ፤ ዘወልዶች ፤ ደም አድራቂ ሽማግሌዎች እና የእርፎ መረባ እናቶች በሚችና በገዳይ ቤተሰቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን ፤ የተረጋጋ ህይወት እንዲኖር እንዲሁም ደም የመመላለስ ሂደት እንዳይኖር ‹‹ እርቅ ይውረድልን ፤ ደም ይድረቅልን ›› በማለት ምርቃናቸውን ያሻግራሉ ። በሚችና በገዳይ ቤተሰቦች መካከል የተከናወነው እርቅ የፀና እንዲሆን በጋብቻ እንዲተሳሰሩ እንዲሁም ግንኙነታቸው በደስታና በሀሴት እንጂ እርቁ ፈርሶና ግጭቱ ተቀስቅሶ በሚፈጠር ሞት እንዳይሆን ይለምናሉ ፤ ይመርቃሉ ። በተጨማሪ የመገዳደሉ ተግባር በቂም በቀል እና በድንገተኛ ምክንያት ሊፈጠር ይችላል ። አበጋሮች ፤ ዘወልዶች ፤ ደም አድራቂ ሽማግሌዎች የግድያውን አይነት በመለየት ለተገዳይ ቤተሰቦች ገዳይ እና የገዳይ ቤተሰቦች ካሳ እንዲክሱ ያስደርጋሉ።

**በሰርግ ወቅት የሚቀርብ ምርቃን**

ሰርግ የሰው ልጅ ከሚያልፋባቸው የህይወት ሽግግሮች ውስጥ አንዱ ነው ። የእርፎ መረባ እናቶች በረድፍ ከተቀመጡ በኋላ ከወገባቸው በታች አንድ ትልቅ ጋቢ በጋራ ለብሰው ይመርቃሉ ። ጋቢውን በጋራ መልበሳቸው ያላቸውን መከባበር ፤ መስማማት፤ መዋሀድ ፤ አንድነት ፤ አብሮነት እንዲሁም አለኝታነትን የሚጠቁም ነው ። ነጩ ጋቢ ደግሞ ያላቸውን ደስታ የሚወክል እሳቤ ነው ።

አስረጂ እንሆ[9] :-

| አውጪ | ተቀባይ |
|---|---|
| እርፎ መረባ | መረባ |
| መቁረቢያህ ትሁን እርፎ መረባ | መረባ |
| መጀመሪያዋ ወንድ ይሁን እርፎ መረባ | መረባ |
| ማርና ወተት እርፎ መረባ | መረባ |
| ሰምና ፈትል እርፎ መረባ | መረባ |
| እሷ እንደ ድመት ትሁን እርፎ መረባ | መረባ |
| አንተ እንደ ወተት ሁን እርፎ መረባ | መረባ |

የምርቃኑ እሳቤ ጥንዶቹ በኑሯቸው ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ መሰናክሎችን በመደማመጥና በመከባበር ስሜት እልባት እየሰጡ እስከ ህይወት ፍፃሜያቸው ድረስ እንዲዘልቁ ‹‹ መቁረቢያህ ትሁን ›› በማለት ይመርቃሉ ፡፡ በትዳራቸው ውስጥ ልጆች እንዲወልዱ የመጀመሪያ ልጃቸው ደግሞ ወንድ እንዲሆን ምኞታቸውን ገልጸዋል ፡፡ በማኅበረሰቡ እይታ ወንድ ልጅ የጀግንነት ፣ ቆራጥነትና የጥንካሬ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል ፡፡ ባልና ሚስት በህይወት ዘመናቸው የሚዋደዱ ፣ የሚግባቡ ፣ የተረጋጉና የሚከባበሩ እንዲሆኑ ‹‹ ማርና ወተት ፣ ሰምና ፈትል ›› ያድርጋችሁ በማለት መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ ፡፡ ማር ጣፋጭ ሲሆን ወተት ደግሞ ውስጥን የማቀዝቀዝ ተግባር አለው ፡፡ ወተት ነጭ ነው ፡፡ ነጭ ደግሞ የደስታ ተምሳሌታዊ ውክልና አለው ፡፡ ሙሽሪት ከድመት ጋር ተነፃፅራ ቀርባለች ፡፡ ድመት መልካም ባህርይ ያላትና ከሰዎች ጋር የምትላመድ እንዲሁም ንፅህናዋን የምትጠብቅ የቤት እንስሳ መሆኗ የሚታወቅ ነው ፡፡ ሙሽሪት የድመትን ተላማጅነት እና ንፅህና ጠባቂነት እንዲትወርስ ተመኝተዋል ፡፡ ይህ ደግሞ ሙሽሪት ከባለቤቷ ፣ ከቤተሰቦቹና ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር የምትግባባና የምትረዳዳ እንዲሁም ቤቷንና አካባቢዋን በንፅህና የምትይዝ ባለሙያ ሚስት እንዲትሆን ያላቸውን ፍላጎት አመላካች ነው ፡፡

በሌላ መልኩ ድመት የወተት ሌባ ትባላለች ፡፡ የወተት ሌባ የተባለችበት ምክንያት ደግሞ ለወተት ያላት ፍላጎት የላቀ በመሆኑ ነው ፡፡ ወተቱ ከተደበቀበት ቦታ ትፈልጋለች ፡፡ ባል በወተት መመሰሉ ፣ድመት ደግሞ የወተት ሌባ መባሏ በሁለቱ መካከል የላቀ መስተጋብር መኖሩን አመላካች ነው ፡፡ ሚስት ባሏን በላቀ ፍቅር የምትወድ ፣ ከጎኗ ቢለያት የማትፈልግ እንዲሁም ከጎኗ ከሌለ በፍለጋ የምትባዝን መሆኗን ማሳያ ነው ፡፡ መራቂዎቹ ለተመራቂዎቹ ‹‹ሰምና ፈትል ›› እንዲሆኑ ተመኝተዋል ፡፡ ሰምና ፈትል የተጣመሩ ናቸው ፡፡ በጋራ ሲሆኑ ይጠነክራሉ ፡፡ ተዋህደው ብርሃን ይሆናሉ ፣ ጨለማን ያጠፋሉ ፡፡ በመጨረሻም ሰምና ፈትል ራሳቸው ይጠፋሉ ፡፡ ባልና ሚስት የሰምና ፈትል ተምሳሌቶች መሆናቸው የሚዋሃዱ እና በጋራ ብርሃን የሚሰጡ መሆናቸውን አመላካች ነው፡፡ ብርሃን የመስጠት ተምሳሌታዊ እሳቤ ለተራቡ ማብላት ፣ ለተጠሙ ማጠጣት፣ ለታረዙ ማልበስ በጥቅሉ በአስቸጋሪ ህይወት ውስጥ ያሉ ሰዎችን የመርዳትን

[9] ቡድን ተኮር ውይይት ሀብሩ ወረዳ 7/6/ 2014 ዓ.ም

የሚገልጽ ነው። ሰምና ፈትል ብርሃን ሰጥተው መጥፋታቸው ደግሞ የሰውን ልጅ የሞት ጉዞ አመላካች ነው።

## ቡና ሲጠጣ የሚከናወን ምርቃን

እናቶች ተጠራርተው ቡና ይጠጣሉ ። ቡናው ከመዝናኛነት ባሻገር በአንድ ላይ ተገናኝተው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ የሚለዋወጡበት ዐውድ ነው ። ከሚወያዩባቸው ጉዳዮች ውስጥ ስለ አባወራ የአያያዝ ብልኃት ፣ ስለ ልጆች አስተዳደግ እንዲሁም ስለ ቤት አያያዝ የሚሉት ይጠቀሳሉ ። ቡናውን በጋራ መጠጣታቸው የጉርብትና ስርዓታቸው ጠንካራ መሆኑንና በመደጋገፍ ህይወታቸውን የሚመሩ መሆናቸውን የሚጠቁም እሳቤ ነው ። ቡናው ከመቀዳቱ በፊት በእድሜ የገፉ ሰዎች ይመርቃሉ። አስረጂ እንሆ[10]

| መራቂ | ተመራቂ |
|---|---|
| ቅሃጀባ --------ቅሃጀባ | ቅሃጀባ |
| ጤናሽን ይስጥሽ | አሜን |
| አዱኛሽ ሙሉ ይሁን | አሜን |
| ልጆችሽ ይደጉልሽ | አሜን |
| ባልሽን ጤና ያድርግልሽ | አሜን |
| አባወራሽ የዋለበት ለምለም ይሁን | አሜን |
| አንቺም ፊትሽ የማይጠቁር ይሁን | አሜን |
| አትጪ አትታጪ ኑሪልን | አሜን |
| ቀየው ሽማግሌ አይጥፋበት | አሜን |
| ቀየው ልጅ የሚቦርቅበት ይሁን | አሜን |
| አባውራሽ ተናግሮ የሚደመጥ ይሁን | አሜን |
| የተጣሉትን የሚያስታርቅ ይሁን | አሜን |
| አዝመራሽ የማያብል ይሁን | አሜን |
| ለራበው የምታበይ | አሜን |
| ለጠማው የምታጠጪ | አሜን |
| ለታረዘው የምታለብሽ ያድርግሽ | አሜን |

ከላይ የቀረበው ምርቃን ትኩረቱ ጤንነትን ፣ ሰላምን ከአዱኛ ጋር ቡና አፍልታ ለሰበሰበቻቸው ሴት የሚመኙበት ዐውድ ነው ። በረከት ያለው እንጀራ፣ የተረጋጋ የትዳር ህይወት፣ ልጆቿ በሰላምና በጤና እንዲያድጉላት ምኞታቸውን የሚገልፁበት ነው። አካባቢዋን የምታደምቅና በበጎ ስም የምታስጠራ ፣ ከጎረቤቶቿ ጋር በሰላምና በመተሳሰብ የምትኖር መልካም ሴት እንዲትሆን ይማፀናሉ።

ባለቤቷ የሰራው እንዲለመልም ፣ የተናገረው በሰዎች ተደማጭና ተቀባይነት ያለው፣ የሚያመርተው ምርት የተትረፈረፈ እንዲሆን ያላቸውን ቀና ፍላጎት በምርቃናቸው ይገልጻሉ። ወደ ቤቷ እንግዶችና ጎረቤቶች ቢመጡ በደስታ የማስተናገድ ልቦና

[10] ቃለ መጠይቅ መሪጌታ መልካሙ አለሙ ፣ ላልይበላ 3/1/2014 ዓ.ም
ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ ገነት አለሙ ፣ ላልይበላ 3/1/2014 ዓ.ም

እንዲኖራት በመሻት ‹‹ አንቺም ፌትሽ የማይጠቁር ይሁን ›› በማለት ምኞታቸውን ይገልጻሉ ፡፡ በህይወት ውስጥ ማጣት ለሚያጣው ሰው መታጣት ደግሞ ለፈላጊው ሰው አስቸጋሪ ይሆናል ‹‹ አትጪ ፣ አትታጪ ፣ ኑሪልን›› በማለት ይመርቃሉ ፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶችን የሚፈቱ ሽማግሌዎች በአካባቢው የሚኖሩበት ፣ የሰፈር ልጆች በሀሴት የሚቦርቁበት እንዲሆን ውስጣዊ መሻታቸውን ገልጸዋል ፡፡ መራቂዎች ተመራቂዋን የራበውን የምታበላ ፣ የጠማውን የምታጠጣ ፣ ለታረዘው የምታለብስ እንዲትሆን ልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይልን ይለምናሉ፡፡

## በአዝመራ ወቅት የሚቀርብ ምርቃን

በአዝመራ ወቅት የሚቀርብ ምርቃን ትኩረቱ የተዘመረው አዝመራ ቡቃያው ያማረ፣ እሸቱ ማራኪ እንዲሁም ምርታማ እንዲሆን ምኞታቸውን የሚገልጹበት ነው፡፡

በዐውድማ ላይ የሚቀርብ ምርቃንን መረጃ አቀባዮቹ እንዲህ ገልጸውታል[11]፡፡ ‹‹የጦጣ ጅራት የመሰለ ማኛ ጤፍ ይስጥህ ፣ በቀዳሙና በቀዳሙ የሚገሳ በሬ ይስጥህ፣ ቀርቀቦ የሚያንደፋድፍ ማሽላ ጆባ እየተባለ ይመረቃል ›› በማለት ገልፀዋል ፡፡ የጦጣ ጅራት ከጤፍ ቁመት ጋር ተነጻጽሮ የቀረበ ሲሆን የጦጣን ረጅምና የሚያምር ጅራት ለጤፍ ቡቃያ ተሰጥቷል ፡፡ ጤፍ ቁመቱ ረጅም ከሆነ ጥሩ ፍሬ ያፈራል ፡፡ የምርት ብዛትን ከጥራት ጋር ዐዋህዶ እንዲሰጣቸው የሚለምኑበት ዐውድ ነው ፡፡ ቀርቀቦ ከበሬ ቆዳ የሚሰራና ለእህል መሰብሰቢያነት የሚያገለግል ነው ፡፡ ማሽላው ጥሩ ፍሬ አፍርቶ ቀርቀቦውን የሚያስጨንቅ እንዲሆን ይመኛሉ ፡፡ በእንሰሳቱ (ከብቶቹ) ላይ መቅሰፍት እንዳይወርድ ይልቁንም እየረቡና እየበዙ እንዲሄዱለት እንዲሁም አርሰው ከፍተኛ ምርት እንዲያስገኙለት በማሰብ ‹‹ በቀዳሙና በቀዳሙ የሚያገሳ በሬ ይስጥህ›› በማለት ይመርቃሉ፡፡

## በቱፍታ ላይ የሚቀርብ ምርቃን

ቱፍታ አንድ ግለሰብ በህይወቱ ጤና እና አዱኛ እንዲያገኝ ፣ ከጊዜውና ከወራቱ ጋር የተስማማ እንዲሆን እንዲሁም በሰላም ውሎ በሰላም እንዲገባ ፣ ክፉ ነገር እንዳይገጥመው በሚል እሳቤ የሚከናወን የምርቃን አይነት ነው ፡፡ ቱፍታን የሚያዘጋጀው ሰው በአሁኑ ወቅት ሰላማዊ ህይወትን የሚኖር ለወደፊቱ ግን መሰናክል እንዳይገጥመው፣ የዘራው እንዲያፈራለትና እንዲባረክለት በማሰብ የሚዘጋጅ ነው ፡፡ የቱፍታ የምርቃን ስርዓት እንዲከናወንለት የፈለገ ግለሰብ በአካባቢው መልካም ምግባር ያላቸውን ሰዎች በመምረጥ እንዲመርቁት መልዕክቱን ያሻግራል ፡፡ ለቱፍታ የመጡት መልካም ምግባር ያላቸው ግለሰቦች ከመስተንግዶው እየተቋደሱ ይመርቃሉ፡፡ አስረጂ እንሆ[12] ፡-

---

[11] ቃለ መጠይቅ አቶ ዳዊት መኮንን፣ ጉባላፍቶ ወረዳ 7/6/2014
ቃለ መጠይቅ አቶ ስጦታው ሞላ ፣ ጉባላፍቶ ወረዳ 7/6/2014
[12] ቡድን ተኮር ውይይት ቆቦ ወረዳ 3/6/2014 ዓ.ም

| መራቂ | ተቀባይ |
|---|---|
| ከዘመኑ ባለ እጣ ሁን | አሜን |
| ጠላትህ ገለል ይበል | አሜን |
| የምታመርተው ሙሉ ይሁን | አሜን |
| የምታሳድገዉ የተባረከ ይሁን | አሜን |
| ቃልህ የማይታበይ ይሁን | አሜን |
| ነገርህ እውነት ይሁን | አሜን |
| ፍርድህ ሙሉ ይሁን | አሜን |
| ቱፍ..........ቱፍ......ቱ | አሜን |

የቱፋታ ምርቃን እሳቤ ተመራቂው ከወቅቱ ጋር እንዲስማማ የሚመኙበት ነው ። ዘመን የብዙ ነገር መዋጃ በመሆኑ ለተመራቂው ምቹ እንዲሆንለት ፣ ቤቱ በበረከት የተሞላ እንዲሆን ‹‹ከዘመኑ ባለ እድል ሁን›› በማለት ያላቸውን ፍላጎት በምርቃን ያሻግራሉ ። የሚያከናውናቸው ተግባራት ፍሬ የሚያፈሩና የተባረኩ እንዲሁም ምርቱ የተትረፈረፈ እንዲሆን ይሻሉ። የቱፋታ የምርቃን ስርዓት ዋነኛው ምኞት ተመራቂዎቹ ዘመን ሲቀያየር ከሚመጣው ዘመን ጋር እንዲስማሙ ፣ ዘመኑ ለእነሱ ግጥማቸው እንዲሆን የሚመኙበት ነው ።

በተለያዩ ዐውዶች ላይ ተናግሮ የመደመጥ ፀጋ እንዲያገኝ እንዲሁም የሚናገረው ቃል ውሸት የሌለበት ይሆን ዘንድ ምኞታቸውን ይገልጻሉ ። በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ምክንያታዊ እንዲሆን ይሻሉ ። በሌላ መልኩ ምርቃን በሀዘን ቤት ይከናወናል ። ‹‹ ከእንግዲህ ወዲህ በዚህ ቤት ሀዘን አይግባ ፣ የደስታ ቤት ይሁን ፣ የመከራ ዳርቻ ያድርግላችሁ ›› በማለት የማፅናኛና የማጠናከሪያ ምርቃን ይመርቃሉ ። ደካሞችን የሚረዳ (ያገዘ) ሰው ‹‹ አባትህን/ሽን ጧሪና ቀባሪ ያድርግህ ፣ እድሜ ይስጥህ ፣ ለቤተሰብህ አገልጋይ ያድርግህ ፣ ጉልበትህን ይባርክልህ ፣ የማታ እንጀራ ይስጥህ ›› የሚል ምርቃን ያሻግራሉ ። እናትና አባቱን የሚያከብር[13] ‹‹ እንጀራ ይውጣልህ ፣ ተባረክ ፣ ክፉ አይንካብን ›› በማለት ይመርቃሉ ። በተለያየ በሽታ ታሞ የተኛን ሰው ‹‹ ህመምህ/ሽ ባህር ውስጥ ይግባ ›› በማለት መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ ። አስታማሚውን ደግሞ ‹‹ ግንባርህ አይቋጠር ›› በማለት ይመርቃሉ። ተመራቂዎች በህይወታቸው ውስጥ መልካም ነገር እንደሚገጥማቸው ያምናሉ።

**የምርቃን ጠቀሜታ**

ምርቃን በማኅበረሰቡ ህይወት ውስጥ የመቅሰፍት መመለሻ ፣ መልካም ነገርን መጎናፀፊያ እንዲሁም ማኅበራዊ መስተጋብርን ማጠናከሪያ መሆኑ ይታመናል።

[13]አባቱን የሚያከብር ልጅ ኀጢአቱ ይሰረይለታል ። እናቱንም የሚያከብራት ልጅ ድልብ እንደሚያደልብ ነው። አባቱን የሚያከብር ልጅ በልጆቹ ደስ ይለዋል ። በሚፀልይበት ቀን ፈጣሪ ይሰመዋል ። አባቱን የሚያከብር ልጅ ዕድሜው ይረዝምለታል ። እግዚአብሔርን የሚሰማ ልጅ እናቱን ያሳርፉታል ። መጽሐፈ ሲራክ (ምዕራፍ3÷3-7

የምርቃንን ጠቀሜታ በሚከተለው መልኩ ተዋግዷል፡፡ እነሱም፡- ማኅበራዊ ፣ ባህላዊ ፣ ስነልቦናዊ ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ፣ አስተዳደራዊ እንዲሁም ተምሳሌታዊ ፋይዳዎች የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### ማኅበራዊ ጠቀሜታ

የምርቃን ስርዓት ሲከወን ውህደታዊ ተግባራትን የሚሻ ሲሆን ምርቃን ከአካል ቅርርቦሽ ባሻገር የልቦና ትስስር የሚፈጥሩበት እንዲሁም በጋርዮሽ ተማፅኖ በረከት የሚሹበት ስርዓት በመሆኑ ማኅበረዊ መስተጋብርን ያጠናክራል ፡፡

ምርቃን በየተራና በቅብብሎሽ የሚከወን ስርዓት ሲሆን አንድነትንና አብሮነትን የሚገልፅ በመሆኑ ማኅበራዊ ማንነትን የመገንባት ሚና አለው ፡፡ ማኅበረሰቡ የተረጋጋ ህይወትን እንዲመራ በማድረግ በኩል አስተዋፅኦው ላቅ ያለ እንዲሆነ ይታመናል ፡፡ በደም ማድረቅ ስርዓት ላይ አበጋሮች ፣ ዘወልዶች ፣ ደም አድራቂ ሽማግሌዎች እንዲሁም የእርፎ መረባ እናቶች የሚችና የገዳይ ቤተሰቦች እንዲታረቁና ሰላም እንዲወርድ የምርቃን ስርዓት መከወናቸው ማኅበራዊ ሚናውን ያጎላል ፡፡ በተሻጋሪነት የሰዎችን ልቦና ዘልቆ የመግባት ሃይል ያለው በመሆኑ ሰዎችን ወደ መልካምነት ፣ ደግነት ፣ አስተዋይነት እንዲሁም ቅንነት የመለወጥ ኃይል አለው ፡፡ ምርቃን ማኅበራዊ ትስስርን ይገነባል ፤ መልካም አስተሳሰብን ያሰፋል እንዲሁም ጠቃሚ የሆኑ ማኅበራዊ እሴቶችን በመትከል ትውልድን የማስተማርን ሚና ይወጣል ፡፡

### ባህላዊ ጠቀሜታ

ምርቃን በተለያዩ ምክንያቶች ሲከወን የአከዋወን ስርዓቱንና ሂደቱን ለተከታዩ ትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ቀጣይነት እንዲኖረው ያስችላል ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች የሚተገበሩ ምርቃኖች ትኩረታቸው ምን ላይ እንደሆነ መለየት ባህልን በማስተዋወቅ በኩል ጠቀሜታ አለው ፡፡ የምርቃን አከዋወን ሂደት ፣ የምርቃን ሰጪዎቹ ማንነት እንዲሁም የምርቃኑ ትኩረት የማኅበረሰብን ወግ ፣ ደንብ ፣ እሴት ፣ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሁም ማኅበራዊ መስተጋብራቸውን የመግለጽ አቅም አለው ፡፡ በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶችና ዐውዶች ምርቃኖች ሲከወን የመራቂዎቹ እና የተመራቂዎቹ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ፣ ቃላዊ ምልልሶች፣ የእጅ መዳፍን እንዲሁም ጉልበትን የመሳም ተግባራት ባህላዊ መሰረት አላቸው፡፡

### ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ

ምርቃን አዱኛዊ እርከንን በማሳደግ በኩል አበርክቶ ያለው ሲሆን የሰው ልጅ በተለያዩ መቅሰፍቶች የአልጋ ቁራኛ ከሆነ በቤተሰብና ሀገር ላይ ጫና ይፈጥራል ፡፡ ማኅበረሰብን ከሚያናጋ አሉታዊ ክስተት ለመሰወር ‹‹ ጤና ይስጥህ ፣ ውለህ ግባ፣ ክፉ አያግኝህ ›› በማለት መመረቃቸው ሰው ከበሽታና ከመቅሰፍት ከተሰወረ በተለያዩ ሙያዎች ላይ ስለሚሳተፍ ለራሱ ፣ ለቤተሰቡና ለሀገር ምጣኔ ሀብታዊ

እድገትን ያመጣል ። የታመሙ ሰዎችም ከህመማቸው እንዲፈወሱ መመረቃቸው ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ አለው፡፡

ምርቃን የተመረቀው ሰው ለበለጠ ደግነትና ታታሪነት የሚያነሳሳ ነው ። እንዲሁም ደካሞችን የመርዳትና ቤተሰቡን የማክበር ልምዱን አጠናክሮ እንዲቀጥልና ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዲፈጠር የማድረግ አቅም አለው ። አበጋሮች ፣ ዘወልዶች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች እንዲሁም የእርፎ መረባ እናቶች በግጭት አፈታት ስርዓት ላይ በሟችና በገዳይ ቤተሰቦች መካከል እርቅ እንዲወርድ እንዲሁም ከታረቁ በኋላ እርቁ የፀና እንዲሆን በቀና ልቦና ይመርቃሉ ። ምርቃኑ አንድም የገዳይ ቤተሰቦች አካባቢያቸውንና የእርሻ መሬታቸውን ጥለው እንዳይሰደዱ ይልቁንም በሰላም ከአንድ ገበያ ላይ የሚውሉበት ፣ ከብቶችን ከአንድ ወንዝ የሚያጠጡበት እንዲሁም በተለያዩ ማኅበራዊ ዐውዶች ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስችል ነው ። የገዳይ ቤተሰቦች ሳይሰደዱ ስራቸውን የሚያከናውኑ ከሆነ ምርታማ በመሆን ልማትን ለማፋጠን ሚና አለው፡፡ የሟች ቤተሰቦች ደም ለመመለስ የገዳይ ቤተሰቦችን በማሳደድ የሚያጠፉትን ጊዜ ለስራ እንዲያውሉት ስለሚያስችላቸው ምርታማ እንዲሆኑ የማድረግ ሚና አለው፡፡ እንዲሁም አዝመራው ለፍሬ እንዲበቃ፣ ምርቱ እንዲትረፈረፍ፣ ከብቶቹ ጋጥ ሙሉ እንዲሆኑ መመረቃቸው ምጣኔ ሀብትን ለማሳደግ ወሳኝ ተግባር አለው ተብሎ ይታመናል፡፡

### ትዕምርታዊ ጠቀሜታ

ምርቃን የተለያዩ ትዕምርታዊ ፋይዳዎች ያሉት ሲሆን በባህል ውስጥ ያሉ ትዕምርታዊ እሳቤዎች በቋንቋ እና በቁስ ተምሳሌታዊ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ትዕምርቶቹን በመተንተን የተለያዩ ሰብዓዊ ጉዳዮችን ማምረት ይቻላል ። የእርፎ መረባ እናቶች ተቀምጠው ከወገባቸው በታች አንድ ነጭ ጋቢ በጋራ መልበሳቸው አንድም ነጭ ጋቢ የብሩህ ተስፋ ፣ የደስታና የስኬት ተምሳሌትነት ገላጭ ሆኖ ይቀርባል ። አንድም አንድ ጋቢ በጋራ መልበሳቸው ማኅበረሰቡ ያላቸውን አብሮነት፣ አንድነትና ውህደት አመልካች ትዕምርት አለው፡፡

በደም ማድረቅ ስርዓት ላይ አበጋሮች ፣ ዘወልዶች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ግጭት ሲፈቱ የእርፎ መረባ እናቶች ዘንግ በእጃቸው ይዘው ምርቃን ማቅረባቸው ከሃይማኖታዊ አስተምሮ የሚቀዳ እሳቤ አለው ። ‹‹ዘንግ››[14] አስቸጋሪ ነገርን ለመሻገሪያነት እንዲሁም እንቅፋትን የማለፊያ ትዕምርት ነው ። ምርቃን እርጥብ ሳር ተጎዝጉዞ መከናወኑ እርጥብ ሳር የመልካም እድል ትዕምርትን የሚገልጽ በመሆኑ መልካም የህይወት ገጽታ እንዲቀናቸው የሚጠቁሙበት ነው ። ምርቃን እድሜያቸው በገፉ ሰዎች መከናወኑ በማኅበረሰቡ ህይወት ውስጥ መከባበር

[14]አንተም በትርህን አንሳ ፤ እጅህንም በባህር ላይ ዘርጋ ፤ ክፈለውም ፤ የስራኤልም ልጆች በባሕር ውስጥ በየብስ ያልፋሉ ። ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 14 ፣16 -17
ሙሳም ፡ ባሕሩን ፡ በበትርህ ምታው ፡ ስንል ፡ ላክንበት ፡ (መታውና) ፡ተከፈለም ፡ ክፍሉም ፡ሁሉ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ጋራ ፡ ኾነ ። አል-ሹዐራ 19፣ 63

የነገሰበት ፣ የሽማግሌዎች ቃልና ተግባር የሚገለጽበት እንዲሁም ማኅበራዊ ደረጃቸውን የመጠቆም ትዕምርታዊ ሚናን ይወጣል ፡፡

## አስተዳደራዊ ጠቀሜታ

በማኅበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ ግጭቶች በሰላም እንዲፈቱና እርቁም መሰረቱ የፀና እንዲሆን ምርቃን ሚና አለው ፡፡ ልጆች ቤተሰቦቻቸውን ፣ በእድሜ የሚበልጧቸውን ወንድምና እህቶቻቸውን እንዲያከብሩ እንዲሁም በእድሜ ለገፉ ሽማግሌዎች የመታዘዝ መንፈስን እንዲያዳብሩ ያስችላል ፡፡ በተጨማሪም ሰላማዊ አካባቢ እንዲኖር እና አጎራባች አካባቢዎች የወንድማማችነትን መንፈስ እንዲገነቡ ፣ ሰዎች ለሰዎች መልካም ተግባራትን በመፈጸም የተረጋጋ ማኅበረሰብ እና ሀገር እንዲኖር የማስቻል ሚና አለው ተብሎ ይታመናል ፡፡ የተመረቁ ሰዎች ለህግና ለደንብ ተገዢ በመሆን ሀገራዊ ልማትን ያፋጥናሉ ፡፡ እንዲሁም ደካሞችን የሚረዱ ፣ ለሰዎች ቅን የሚያስቡ .፣ ለቂም በቀልና ለአመፅ የማይነሳሱ ይልቁንም ለፍቅርና ለአንድነት ትልቅ ቦታ የሚሰጡ ሰዎች እንዲኖሩ የማስቻል አቅም አለው፡፡

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የምርቃን ስርዓተ ከበራ ኃይል በሰሜን ወሎ ማኅበረሰብ በሚል ርዕስ የተጠና ነው ፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የምርቃን ማኅበረ- ስነልቦናዊ ፋይዳን መመርመር ነው ፡፡ ዓላማ ተኮር ናሙና ፣ ገላጭ ምርምር እንዲሁም ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ ግልጋሎት ላይ ውለዋል ፡፡ ምርቃን ጥንታዊነት ያለው ሲሆን በማኅበረሰቡ ውስጥ የተወለደና ያደገ የስነ ቃል አይነት ነው ፡፡ መራቂዎች ለተመራቂዎች የዘሩትና የወለዱት እንዲባረክ ፣ ከመቅሰፍትና መከራ እንዲሰወሩ እንዲሁም ሀብትን እንዲጎናጸፉ የሚመኙበት ስርዓት ነው ፡፡ ምርቃን አመክንዮ ተኮር ሲሆን እና እውነታ ላይ ሲመሰረት በልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል ቅቡል እንደሆነ ይታመናል፡፡

ምርቃን ከሚከወኑባቸው ዐውዶች ውስጥ ልጅ ሲወለድ ፣ አዲስ ቤት ተሰርቶ ሲገባ፣ በግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ፣ በእርሻ ስራ ላይ ፣ በሰርግ ፣ ቡና ሲጠጣ እንዲሁም በቱፋታ ዐውድ ላይ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የምርቃን ስርዓት ከሚከወንባቸው ምክንያቶች ውስጥ ግጭትና ጦርነት እንዳይከሰት፣ ድርቅ እንዳይሆንና ወረርሽኝ እንዳይመጣ ፣ የታመሙ ሰዎች ከህመማቸው እንዲፈወሱ ፣ ምጥ የተያዙ እናቶች በሰላም እንዲገላገሉ፣ ዝናብ በወቅቱ እንዲመጣ፣ እርቅ እንዳይፈርስና እንዲፀና ፣ አዲስ የተሰራ ቤት መደሰቻ እንዲሆን ፣ ትዳር መስራቾች ትዳራቸው መልካም እንዲሆንና ልጆች ወልደው የሚስሙ እንዲሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ የምርቃት ስርዓት የሚመራው በሀይማኖት መሪዎች ፣ በአበጋሮች ፣ ዘወልዶች ፣ ደም አድራቂ ሽማግሌዎች እንዲሁም በእርፎ መረባ እናቶች አማካኝነት ነው፡፡ ምርቃን ማኅበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም ምጣኔ ሀብታዊ ፍይዳዎችን የማበርከት ኃይል አለው፡፡ ሆኖም ግን ምርቃን ለልማት እንዲውል ከማድረግ አኳያ ውስንነት ይታያል፡፡ በመሆኑም የሀገር ሽማግሌዎች ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

እንዲሁም የባህል ተመራማሪዎች ምርቃን ለልማት እንዲውል ከማድግ አኳያ በአጽንኦት ቢሰሩ ጥሩ ነው።

## ዋቢ ጽሑፎች

ቅዱስ ቁርኣን (የአማርኛ ትርጉም) ፡፡ 1997 ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ነጃሺ አሣታሚ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፡፡ 1980 ፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ ፡ የብሉይና የሃዲስ ኪዳን መጻሕፍት* ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፡፡

ያለው እንዳወቀ ፡፡ 2009 ፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርህዎችና አተገባበር* ፡፡ ባሕር ዳር፡ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

Assefa Balcha .2017. Wadaja Ritual: Portrait of a Wallo Cultural Coping Mechanism, Eastern African Literary and Cultural Studies, 3:1, 40-52, DOI:10.1080/23277408.2017.1323170

Barnhart, Robert K.1995. *The Barnhart concise dictionary of Etymology*. Harper Conllins.

Derek, Prince. 1994. “ Explaining Blessing and Curses.” Nelson World Ltd. 9 Holdon Avenue, Bletchley, Milton Keynes, England.

Hurreiz Sayyied. 2006. *Study in Africa applied Folklore.* African university congress Publisher , Khartoum.

Nizita, Richard. 1993. *People and Cultures of Uganda*. Fountain Publishers . Ltd.

Okpewho, lsidore.1992. *African oral Literature Backgrounds, character ,and continuity*. Indiana university press.

Patricia, Annlynch. 2004. *African mythology A to Z.* New York.

Sims, M. C.&Martine stephens. 2005. *Living Folklore* :*An introduction to the Study of people and their traditions*. Logan, Utah State university press.

Tzadok, Bar Rabbi Ariel. 2000. “ Blessing and Curse : How much is in our own Hands? ” Commentary to Parashat Kitaw.